

## ሳምሶን

- እስራኤላውያን ከጠላቶቻቸው እጅ የሚያድናቸውን ሰው ይፈልጉ ነበር። የጌታ መልአክም ማኖሄ ለሚባል ለአንድ ፃድቅ ሰው ሚስት ተገለጠ። ወንድ ልጅ እንደምትወልድም ነገራት። የሚወልዱት ልጅም የወይን ጠጅ መጠጣት እንደሌለበትና ፀጉሩንም መቆረጥ እንደማይገባው ነገራት። ይህም የናዝራዊነት ኪዳን ተብሎ ይታወቃል። ሳምሶንም ኪዳኑን ጠበቀ። የእግዚአብሔር መንፈስም ወደእርሱ መጣ። እጅግ ብርቱ ነበር። እጅግ ብርቱ ከመሆኑ የተነሳም በአህያ መንጋጋ ብቻ ተዋግቶ  አሸንፎ ያውቃል። ያለምንም መሣሪያ በባዶ እጁ የአንበሳ ደቦል ገደለ። እንዲሁም በአንድ ወቅት በጣም ከባድ የሆነውን የከተማይቱን መዝጊያ ተሸክሞ ወደ አንድ ኮረብታ  ሄዷል።

- ሆኖም ሳምሶን ደሊላ የተባለች ፍልስጥኤማዊት ሴት አፈቀረ። ጠላቶቹም እሱን ለማሸነፍ ደሊላን ተጠቀሙባት። በእርሱ ውስጥ ያለው ኃይል ምስጢር ምን እንደሆነ አውቃ ከነገረቻቸው ብዙ ብር እንደሚሰጧት ቃል ገቡላት። በመጀመሪያ የኃይሉ ምስጢር ምን እንደሆነ ስትጠይቀው ሶስት የተለያዩ ነገሮችን ነገራት። ሶስቱም ነገሮች እውነት አልነበሩም። በመጀመሪያ የነገራት ባልደረቀ በእርጥብ ገመድ ብታሰር ኃይሌን አጣለሁ ብሎ ነገራት። እንደገናም ምንም ስራ ባልተሰራበት አዲስ ገመድ ብታሰር ኃይሌን አጣለሁ አላት። ይህኛውም እውነት አልነበረም። ሶስተኛው ውሸትም የራሴን ፀጉር ሰባቱን ጉንጉን ከድር ጋር ብትጐነጕኚው፣ በችካልም ብትቸክዪው፣ ኃይሌን አጣለሁ አላት።

- በመጨረሻም እውነቱን ነገራት። የኃይሉ ምስጢር ፀጉሩና የናዝራዊነት ኪዳኑ እንደሆነ ነገራት። ኃይለኛ እንቅልፍ እንዲይዘው ካደረገች በኋላም ፍልስጥኤማውያን መጥተው ሰባቱን የሳምሶንን የፀጉር ጉንጉን ላጩ።

ከእንቅልፉም ሲነቃ ኃይሉ ከእርሱ መራቁና መድከሙ ታወቀው። ራሱንም መከላከል አልቻለም። አይኑን ካወጡት በኋላም እስረኛ አድርገው ወሰዱት፤ ባሪያም አድርገው ማሰራት ጀመሩ።

❋ ፀጉሩ እንደገና መብቀል ሲጀምርም እግዚአብሔር እንደገና ኃይል እንዲሰጠው ለመነ። ከዚያም በሳምሶን ላይ ሊሳለቁበትና ሊዝናኑበት ፈልገው ለአምላካቸው ለዳጎን መስዋዕት ለማቅረብ ወደተሰበሰቡበት ትልቅ ሕንፃ አመጡት። ሕንፃው ሲደረመስም ሳምሶን ከፍልስጥኤማውያን ጋር አብሮ ሞተ።

*የሳምሶን ታሪክ የሚገኘው በብሉይ ኪዳን በመፅሐፈ መሳፍንት ምዕራፍ 13-16 ውስጥ ይገኛል።*

http://gardenofpraise.com